AABE
Accounting and Auditing Board of Ethiopia
የኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ

ከኢትዮጵያ የሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

ኢኮኖሚ

# የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውጤታማነት ለኢኮኖሚ ዕድገት

በሀገራችን የዓለም አቀፍ ፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ደረጃዎችን ተቀብሎ በሥራ ላይ ማዋል የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ዕድገት አምቅ አቅም ለመጠቀምና አጠናክሮ ለማስቀጠል ያስችላል። እንዲሁም የፋይናንስና የኦዲት ሪፖርት ደረጃዎችን በመተግበር ኢንቨስተሮች በሀገሪቱ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ሥርዓት ላይ የሚኖራቸውን አመኔታ ያሳድጋል። ከዚህ በተጨማሪ ኢንቨስትመንትን በመሳብ የኢኮኖሚ እድገቱን የሚያስቀጥል ከመሆኑ ባሻገር፣ የኢኮኖሚ መረጋጋትን፣ ውጤታማ የሀብት አስተዳደርን፣ ግልፀኝነትና ተጠያቂነትን በማስፈን በግልና በመንግሥት ዘርፍ ላይ የፋይናንስ ቀውስ እና የድርጅቶች ውድቀት እንዳይከሰት ያደርጋል። የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድም ይህን ተልዕኮ በስኬታማነት ለመምራት እና ለማስተባበር በህግ የተቋቋመ የመንግሥት ተቋም ነው።

ቦርዱ «ጉልህ የሕዝብ ጥቅም ያለባቸው» ብሎ ከለያቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት መካከል የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ዋነኞች ናቸው። የልማት ድርጅቶቹ ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ ዓመታዊ የሂሳብ መግለጫዎቻቸውን በሙሉ ዓለምአቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት አዘጋጅተው እና ኦዲት አስደርገው ወደ ቦርዱ ማቅረብ እና ለማንኛውም የፋይናንስ ሪፖርት ፈላጊ አካል ፋይናንስ እና ፋይናንስ-ነክ መረጃዎቻቸውን ይፋ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል። ይህንና የልማት ድርጅቶቹን ዋነኛ ዓላማ አስመልክቶ ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታ እና አስተዳደር የኮርፖሬት ገቨርናንስ እና ፋይናንስ ሥርዓት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ወ/ሮ መጠሪያሽ ኃይለጊዮርጊስ ጋር ያደረግነውን ቃለ-ምልልስ እንደሚከተለው አሰናድተናል፤ መልካም ንባብ።



በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታ እና አስተዳደር የኮርፖሬት ገቨርናንስ እና ፋይናንስ ሥርዓት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ወ/ሮ መጠሪያሽ ኃይለጊዮርጊስ

### 1. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች መቋቋም ዋነኛ ዓላማ ምንድነው?

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች መቋቋም ዋነኛ ዓላማ በሀገራችን የገበያ ጉድለት ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ዕድገት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽእኖ ለመቀነስና በግሉ ዘርፍ የማይሸፈኑ ነገር ግን ለሀገሪቱ ዕድገት ወሳኝ በሆኑ ዘርፎች ላይ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተቋቁመው የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ የማድረግ ዓላማን ለማሳካት ነው።

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር የልማት ድርጅቶቹ ተልዕኳቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል በቅርበት እንዲከታተልና እንዲደግፍ በደንብ ቁጥር 445/2011 የተቋቋመ ሲሆን በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 25/1984 በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ድርጅቶችን የሚመራ የሥራ አመራር ቦርድ መድቦ የልማት ድርጅቶችን ከተሰጣቸው ተልዕኮ አንጻር፣ በስትራቴጂ እና በቢዝነስ እንቅስቃሴ መካከል ያለውን ትስስር፤ ያላቸውን ምርታማነት፣ ተወዳዳሪነትና የገበያ ስትራቴጂ፤ የፕሮጀክት አመራርና ኮንትራት አስተዳደር፤ የኮርፖሬት ገቨርናንስ እና የኮርፖሬት የፋይናንስ ሥርዓታቸውን በመከታተልና በመደገፍ የልማት ድርጅቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋል። በዚህ መሠረት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር የሚከተሉትን አምስት ዋና ዋና ዓላማዎች ለማሳካት ይሠራል፤

I. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውጤታማ፣ ተወዳዳሪና አትራፊ እንዲሆኑ ዘመናዊ የኮርፖሬት አስተዳደርና የኮርፖሬት ፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋትና ሥራ ላይ መዋሉን መከታተል፤
II. የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አመራርና አስተዳደር መከታተል፤
III. የመንግሥት የልማት ድርጅቶችና አክሲዮን ማህበራት ውስጥ መንግሥትን በመወከል የመንግሥትን የባለቤትነት መብት ማስከበር፤
IV. የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን አስተዳደር የመንግሥት የባለቤትነት፣ የተቆጣጣሪ እና የፖሊሲ አውጪውን አካላት ኃላፊነትና ሚናን በለየ መልኩ መተግበሩን ማረጋገጥ፤ እና
V. በመንግሥት የልማት ፖሊሲ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ስምሪት መካከል የሚኖረውን ቅንጅት ማሳለጥ ነው።

### 2. በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት እና የሕዝብ ተጠቃሚነት ላይ ያላቸው ሚና ምን ይመስላል?

በሀገራችን በመንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደሩ በርካታ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ያሉ ሲሆን እስከ 2014 በጀት ዓመት መጨረሻ (የተወሰኑ ድርጅቶች ወደ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ እንዲዛወሩ ከመደረጉ በፊት) አብዛኛዎቹ የልማት ድርጅቶች ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ተጠሪ ነበሩ። የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በተለያየ የንግድ ዘርፍ ተሰማርተው የሚሠሩ ሲሆኑ እንደሚያስተዳድሩት ሀብት መጠን ይለያያሉ። ሁሉም የልማት ድርጅቶች በሕግ የተሰጣቸውን ተልዕኮ ለማሳካት እስትራቴጂ እና ዓመታዊ ዕቅድ ነድፈው ውጤታማ እና አትራፊ ለመሆን ይሠራሉ። የልማት ድርጅቶቹ ተገቢውን አመራርና አስተዳደር ካገኙ ውጤታማና አትራፊ ስለሚሆኑ ለሀገር እና ለሕዝብ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያበረክታሉ። በየበጀት ዓመቱ በሚያደርጉት የንግድ እንቅስቃሴ ከሚያገኙት ትርፍ ልዩ ልዩ የመንግሥት ግዴታዎችን የሚወጡ /ለምሳሌ ታክስ፣ የመንግሥት የትርፍ ድርሻ መክፈል፣ ወዘተ./ ሲሆን ይህም የመንግሥትን ከፍተኛ ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ ይውላል። የልማት ድርጅቶች ለዜጐች የተለያየ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ እንዲሁም የኮርፖሬት ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት የማኅበረሰቡን ችግሮች የሚቀርፉ ሥራዎችን በጀት መድቦ በማከናወን ድጋፍ የሚያደርጉ ናቸው።

### 3. ግልፅ እና ተዓማኒ የፋይናንስ ሪፖርት መረጃዎችን ለመረጃ ፈላጊ አካላት ከማቅረብ አንፃር የልማት ድርጅቶቹ አሠራር እንዴት ይገለፃል?

አስተዳደሩ የልማት ድርጅቶች አሠራሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቃኘ እንዲሆን ለማድረግና የድርጅቶችን ቀጣይ ዕድገትና ተወዳዳሪነትን ለማስፋት ወጥና ዘመናዊ የኮርፖሬት ገቨርናንስ እና የፋይናንስ አሠራር ሥርዓት እንዲከተሉ አድርጓል። የኮርፖሬት ገቨርናንስ ኮድና ኮዱን ተከትለው የወጡ አስራ ሦስት/13/ የተለያዩ የኮርፖሬት ገቨርናንስ እና የፋይናንስ ሥርዓቶችን በልማት ድርጅቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ በማድረግ በመከታተልና በመደገፍ ላይ ይገኛል። አስተዳደሩ የወጡ ሥርዓቶች ተፈጻሚነትንም የሚለካበት የኮርፖሬት ገቨርናንስ ሥርዓት ስኮር ካርድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ተደርጓል። በዚህ የመለኪያ ሥርዓት የልማት ድርጅቶች የኮርፖሬት ገቨርናንስ እና ፋይናንስ አሠራር ሥርዓት አፈጻጸም ተለክቶ አስፈላጊው ማስተካከያ እየተደረገ ይገኛል።

ከተዘረጉ የአሠራር ሥርዓቶች መካከል የልማት ድርጅቶች የዲስክሎዥር መመሪያ ይገኝበታል። ይህ የዲስክሎዥር መመሪያ የልማት ድርጅቶች ግልጽና ተአማኒ የሆኑ የፋይናንስ ሪፖርቶችን ለባለድርሻ አካላት ወቅቱን ጠብቀው ይፋ እንዲያደርጉ ግዴታ የሚያስቀምጥ ሲሆን በዚህ መሠረት የልማት ድርጅቶችም መረጃዎችን ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲያደርጉ እየተሠራ ይገኛል። ተአማኒ የሆኑ የፋይናንስ መረጃዎችን በተለያዩ የመረጃ ማሰራጫ ዘዴዎች ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ውስንነት ቢኖርም የተሟላ እንደሆን ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል።

በተመሳሳይም የኢትዮጵያ መንግሥት በሀገሪቱ ባሉ በሁሉም የግል፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ባልሆኑ የልማት ድርጅቶች ላይ ተግባራዊ የሚደረግ ግልጽ እና ተዓማኒ የሆነ ማንም በቀላሉ ሊረዳው የሚቻል ዓለምአቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ ደረጃዎችን በአዋጅ ቁጥር 847/2006 ባፀደቀው መሠረት እና ቦርዱም ባወጣው የትግበራ ፍኖተ-ካርታ መሠረት የልማት ድርጅቶች የመጀመሪያ ተግባሪዎች እንደመሆናቸው መጠን ወደ ትግበራ ገብተዋል።

በዚሁም መሠረት በአሁኑ ጊዜ ለአስተዳደር መሥሪያ ቤቱ ተጠሪ ከሆኑ ዘጠኝ የልማት ድርጅቶች መካከል ስምንቱ በሙሉ ከ2010 በጀት ዓመት ጀምረው የፋይናንስ ሪፖርታቸውን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች(IFRS) ያዘጋጁ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ሦስት የልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን ወቅታዊ በማድረግ ለኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ሪፖርታቸውን አቅርበዋል። ሌሎችም ሙሉ የትግበራ ሂደት ያጠናቀቁ ሲሆኑ ዓመታዊ ሂሳባቸውን በውጭ ኦዲተር አስመርምረው የተለያየ የበጀት ዓመት ሪፖርት አቅርበዋል። እንዲሁም አንድ በIFRS ትግበራ ሂደት ላይ የሚገኝ የልማት ድርጅት ትግበራውን አጠናቆ ለምርመራ የሚያቀርብ ሲሆን ሁሉም ተጠሪነታቸው ለአስተዳደር መስሪያ ቤቱ የሆኑ የልማት ድርጅቶች ሙሉ IFRS ትግበራ አከናውነዋል ማለት ይቻላል።

### 4. የአስተዳደሩ የክትትል፣ ቁጥጥር እና ድጋፍ ሥርዓት እና የልማት ድርጅቶቹ አሁን ያሉበት የትግበራ ሂደት ምን እንደሚመስል ቢያብራሩልን?

አስተዳደር መሥሪያ ቤቱ በአሁኑ አዲስ መዋቅር ከመዋቀሩ በፊት በሚኒስቴር ደረጃ እያለ ሁሉም የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ተጠሪነታቸው ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በመሆኑ ሁሉም የልማት ድርጅቶች ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራርብ ደረጃዎች መተግበር ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር መሆኑን በማመን ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ ክትትልና ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል።

ከመነሻው ጀምሮ ለልማት ድርጅቶች ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፣ የፋይናንስና የኦዲት ክፍል ኃላፊዎች ከሂሳብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ጋር በመተባበር ለተለያዩ ጊዜያት ለአምስት ቀናት የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራርብ የትግበራ ደረጃዎች ስልጠና ተሰጥቷል። ለድርጅቶች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በራሳቸው በድጋሚ ጥልቅ ስልጠናዎች እንዲሰጡ ክትትል ተደርጓል።

የልማት ድርጅቶች የውጭ አማካሪ ቀጥረው ትግበራውን እንዲጀምሩ አቅጣጫ ተሰጥቶ ተፈጻሚነቱ ክትትል ተደርጓል። አማካሪ የመቅጠር አቅም ለሌላቸው አራት ድርጅቶች በአስተዳደሩ በኩል ወጪያቸው ተሸፍኖላቸው ቅጥር እንዲፈጽሙ ተደርጓል።

አስተዳደሩ በስሩ የሚያስተዳደራቸውን የልማት ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ ጋር በመቀናጀትና ታክስ ፎርስ በማቋቋም ለሦስት ጊዜ በመስክ ተገኝቶ የአፈጻጸም ደረጃቸው ተገምግሟል፤ ሙያዊ ድጋፎችም ተደርገዋል።

በመስክ ምልከታና ከድርጅቶች ከሚቀርቡ የድጋፍ ጥያቄዎች በመነሳት ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት ለትግበራው እንደማነቅ የቀረቡት ጉዳዮችን እንዲፈቱ አቅጣጫ በማስቀመጥና ሙያዊ እገዛ እንዲያገኙ በማድረግ ችግሮችን ለመፍታት ተችሏል።

### 5. ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች (IFRS) መሠረት ቀድመው የተገበሩም ይሁን አሁን በትግበራ ላይ ያሉ ድርጅቶች በሂደቱ ምን ምን ተግዳሮቶች አጋጥመዋቸዋል? የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች ካሉ?

❖ **መልካም ተሞክሮ**

- የፋይናንስ ሥርዓቱ እንደሀገር ተግባራዊ መደረጉ ጠቀሜታውን የተገነዘቡ ድርጅቶች ፈጥነው አማካሪ በመቅጠር መተግበር በመቻላቸው ከእነሱ ሌሎች የልማት ድርጅቶች ልምድ እንዲቀስሙ ተደርጓል፤
- ትክክለኛ ሀብት እና ዕዳቸውን ለይተው ሊያሠራቸው እና ቀጣይነታቸውን ሊያረጋግጥላቸው የሚችል ሥርዓት መዘርጋት እና መመራት ተችሏል፤
- የልማት ድርጅቶች የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸውን ሀብቶች ይዘው እንዲቀጥሉ አስችሏቸዋል።

❖ **ተግዳሮቶች**

- እንደ ሀገር የተቀበልነው አዲስ የፋይናንስ ሥርዓት በመሆኑ የልማት ድርጅቶች ጠቀሜታውን ተገንዝበው ለመተግበር ጊዜ መውሰዱ፤
- በIFRS የትግበራ ደረጃዎች ዙሪያ የነበሩ ስልጠናዎች ውስን መሆን፤
- የልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን በወቅቱ ከመዝጋት አኳያ በአማካይ የ3 ዓመታት የተጠራቀመ (ባክሎግ) መኖር፤
- በድርጅቶች የቆዩ ሂሳቦች የታሪክ መረጃ አለመገኘት፤ በምርመራ ላይ ያሉ የድርጅቶች ሂሳብ የምርመራ ሂደቱ በወቅቱ ተጠናቆ ሪፖርት አለመቅረቡ፤
- በሀገራችን የንብረት ትመና ባለሙያዎች ውስን መሆኑ፤ በሀብት ትመና ዙሪያ የግንዛቤ ክፍተት መኖሩ፣ የሀብት ዋጋ ትመና ለመሥራት የንብረት ወቅታዊ ዋጋ በቀላሉ አለመገኘቱ፤ /ለምሳሌ የመሬት የሊዝ ዋጋ/፤
- የድርጅቶች የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ውስንነት፤ በIFRS የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍልሰት፤
- በተወሰኑ የልማት ድርጅቶች የአማካሪ ቅጥር መቀያየር፤ አቅም ያለው አማካሪ ለመቅጠር የፋይናንስ እጥረት ማጋጠሙ፤
- የልማት ድርጅቶች ተግብረው ለቦርዱ የሚያቀርቡት የሂሳብ ሪፖርት ምርመራ እና ኦዲት ጥራት የሚያረጋግጠው አካል ምላሽ ፈጣን አለመሆኑ።

### 6. በቀጣይ ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ?

በቀጣይ እንደሀገር የልማት ድርጅቶች IFRS ተግብረው ወደ ቦርዱ ማቅረብ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑ በተለይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ማለትም የኢትዮጵያ ሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን በደረጃዎቹ መሠረት ተግብረው ሲያቀርቡ ግብረ-መልስ ከመስጠት አኳያ እና የፋይናንስ ባለሙያዎችን ለማፍራት ከስልጠና ማዕከላት ጋር በጋራ መሥራት ያስፈልጋል። የኦዲት ሰርቪስ ኮርፖሬሽን የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ የመንግሥትን ሀብት የሚያንቀሳቅሱ እንደመሆናቸው መጠን ሂሳብ ዘግተው ለምርመራ የሰጡትን ሂሳብ በወቅቱ መርምሮ የኦዲት ውጤቱን ማሳወቅ ይገባቸዋል። የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር የልማት ድርጅቶች ሂሳባቸውን በአዲሱ ስታንዳርድ ዘግተው ለምርመራ እንዲሰጡ በመከታተልና በመደገፍ እንዲሁም የሂሳብ ምርመራ ውጤቱን ተቀብሎ የልማት ድርጅቶች የግኝት ማስተካከያዎች እንዲያደርጉ በማድረግ ተናበውና ተቀናጅተው ቢሠሩ የልማት ድርጅቶች ወቅታዊና ደረጃውን የጠበቀ የፋይናንስ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል።

### 7. በተጨማሪ የሚገልጹት ሀሳብ ካለ?

እንደአጠቃላይ በሀገራችን ያሉ ሁሉም የንግድ ተቋማት ሂሳባቸውን በIFRS ተግብረው ሪፖርት እንዲያቀርቡ የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ሲሆን በሀገራችንም በዚህ ሙያ የተሰማሩ በርካታ ባለሙያዎችን ለማፍራት የስልጠና ማዕከላትን በማጠናከር የአካውንቲንግ ሙያውን ማሳደግ አስፈላጊ ይሆናል።

**ስለጊዜዎት እናመሰግናለን!**

እኔም አመሰግናለሁ።